*** ሴቶች በኢየሱስ አገልግሎት *** በ'ወንጌላዊ' ሳሂህ

ከብዙ በታሪክ ካለፉ ሰዎች በተለየ መልኩ ኢየሱስ ሴቶችን አስመልክቶ የነበረው አገልግሎት ቀልብ የሚስብ ነበር። ሁሉም ምሁራን ማለት በሚቻልበት ደረጃ ኢየሱስ ለሴቶች የሰጠውን አገልግሎት ያጠኑ ሁሉ በአድናቆት ነው የሚፅፉት።

እጅግ የሚገርመው ደግሞ የኢየሱስን ለሴቶች የሰጠውን ቦታ አስመልክቶ በአድናቆት የፃፉት በመለኮትነቱ የሚያምኑ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ መለኮትነቱን የሚክዱ እንደ ይሆዋምስክሮች ያሉ የእምነት ቡድኖችም ጭምር መሆኑ ነው። 'መፅሀፍ ቅዱስ ምን ያስተምረናል?' በሚል ርዕስ የታተመው የመጠበቂያግንብ ማህበር መፅሀፍ እንዲህ ይላል፦

'ኢየሱስ ምድር ላይ በኖረበት ዘመን ሴቶች ምንም መብት አልነበራቸውም፤ ሰዎች ይንቋቸው ነበር። ኢየሱስ ግን ለሴቶች አክብሮት ነበረው!'(1)

ኢየሱስ በእርግጥ ሴቶችን ከወንዶች ባነሰ መልኩ ይመለከታቸው የነበረ ቢሆንና በአገልግሎቱም አሳንሷቸው ቢሆን ኖሮ አምላክነቱን/መለኮትነቱን/ ለመተቸት አመቺ ስለሚሆን ከመጠበቂያ ግንብ በላይ መረጃውን የሚያራግበው አካል አይኖርም ነበር። ነገር ግን አገልግሎቱ በተቃራኒው ለሴቶች ክብርን በሰጠና ባስቀደመ መልኩ ስለነበር ድርጅቱ እየጎመዘዘውም ቢሆን ከላይ ያለውን ምስክርነት ለመስጠት ተገዷል።

ኢየሱስ ለሴቶች የሰጠውን ቦታ በትክክል ለመረዳት ኢየሱስ በነበረበት ጊዜና አካባቢ ሴቶች የነበራቸውን ቦታ መዳሰሱ ወሳኝነት አለው። በመሆኑም በመጀመሪያው ክ/ዘ ሴቶች በአይሁዳዊያን እንዴት ይታዩ እንደነበር የተወሰኑ ማሳያዎችን እንመልከት።

እንደ ምሁራን አስተያየት ከሆነ በመጀመሪያው ክ/ዘ አይሁዳዊያን ዘንድ ሴቶች ከወንድ ያነሰ ቦታ ብቻ ሳይሆን ያላቸው ጨርሶውኑ እንደ ሙሉ ሰውም አይታዩም ነበር።የወንጌል ፀሀፊያን በሆኑት እንደተገለፀው ከሆነ በህዝብ ቆጠራ ወቅት እንኳን የወንዶቹ ብዛት ሲቆጠር ሴቶች ሙሉ ሰው ተደርገው ካለመቆጠራቸው የተነሳ በቆጠራው ከግምት አይካተቱም ነበር። በእርግጥም አይሁዳዊያኑ ስለ ሴቶች የነበራቸው አመለካከት ይህ ነው ተብሎ የሚጠቀስም አይደለም።

በአይሁዳዊያኑ ዘንድ ሴቶች እንደ ቆሻሻ ከመቆጠራቸው ባለፈ የሀጢያት ምክንያት ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብም የዘመኑ የሀይማኖት መምህራን የሆኑት ፈሪሳውያን ሴቶችን አይተው በሀጢያት ላለመሰናከል በማሰብ አቀርቅረው ነበር የሚሄዱት። ከዚህም የተነሳ ብዙ ጊዜም በመንገድ ዳር ከቆሙ ግዑዛን ቁሶች ጋር እየተጋጩ ራሳቸውን እስከመጉዳት ሁሉ ይደርሳሉ(2)

በዚሁ ዘመን የነበሩ ሴቶች የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ይቅርና ለመማር እንኳን የተገባቸው ተደርገው አይታዩምም ነበር። ታላቁ የአይሁድ መምህር ራቢ ኤሊዘር እንዲህ

ይላል፦ 'የህጉ ቃል ለሴቶች ከሚቀርብ ይልቅ በእሳት ቢቃጠል ይሻላል'(3)

ይህ ብቻም አይደለም በጊዜው በአደባባይ ከወንዶች ጋር ሴቶች እንዲያወሩ አይፈቀድላቸውምም ነበር። ታዲያ ይህን ህግ ተላልፈው ከተገኙ የሚጠብቃቸው ቅጣት በማናቸውም ሰዓት ባልየው ጥሎሿን ሳያሟላላት እንዲፈታት ይደረግ ነበር(4)

በአጭሩ ሴቶች ከመናቃቸው የተነሳ የመጥፎ ነገሮች ተምሳሌት ሆነውም ይቀርቡ ነበር። አበራ አዋኖ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያው በፃፈው ጥናቱ እንደገለፀውም ከሆነ ሴቶች በአይሁዳዊያኑ ዘንድ የከንቱ አስተሳሰብ፣ የጠንቋይ፣ የስግብግብነት፣ የግብዝነትና የስንፍና ሞዴል ተደርገው ሁሉ ይቀርቡም ነበር(5).

ስለሆነም ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች ተነስተን ደግሞ ሴቶች በመጀመሪያው ክ/ዘ በነበሩ አይሁዶች ዘንድ የነበራቸው ቦታ በእጅጉን ያነሰ ነው ማለት እንችላለን። እንግዲህ የዚህ ማህበረሰብ አንድ አካል የሆነው ኢየሱስ ስለ ሴቶች በዚህን ያህል የወረደ አመለካከት ባላቸው ሰዎች ዘንድ ሲኖርና ከእነርሱ የተለየ አመለካከት ሲያራምድ ምን ሊገጥመው እንደሚችል ማሰቡ ከባድ አይሆንም። አንድ ማህበረሰብ እንደ ቀኖና የሙጥኝ ብሎ የያዘውን አመለካከት ለመቀየር መሞከርም ቀላል ትዕግስት እና ትግል እንደማይጠይቅም ለማናችንም የሚጠፋ አይሆንም። ይህ ቢሆንም ግን ተዓማኒ ምንጮች እንደሚመሠክሩት ከሆነ ኢየሱስ በዘመኑ ለሴቶች የነበረውን የተንሻፈፈ አመለካከት ከትምህርቱ በተጨማሪም በተግባሩም ታግሎታል፤ ኮንኖታልም።

እንደ ምሳሌም፦ ኢየሱስ በወቅቱ ከነበረው የአይሁድ ወግ በተቃራኒ ከሴቶች ጋር ማውራት ብቻ ሳይሆን ለሴቶች ያልተፈቀደውን ሀይማኖታዊ ትምህርትም አስተምህሮአቸዋል(ሉቃስ10:38-42)፤ ከሰማርያዊቷ ሴት ጋር በአደባባይ ስነመለኮታዊ ጉዳይ ላይ አውግቷል(ዮሐ4:4-42)፤ ኢየሩሳሌምን በኮነነበት ንግግሩ ራሱን በሴት ዶሮ መስሏል(Math23:27, ሉቃ13:34)፤ ተግባራዊነቱ ከወንድ ይልቅ ለሴቷ ጎጂ የሆነውንና በጊዜው በነበሩ አይሁዳዊያን ዘንድ ልማድ የነበረውን መድብለጋብቻ(polygamy) እና በሰበብ ባስባቡ ሚስትን የመፍታት ልማድ(divorce) በትምህርቱ ተቃውሟል(ማቴ5:31-32፣ 27-30, 19:3-9, ማር10:2-12, ሉቃ16:18)፤ ሴቶችን ማሸማቀቅ እንደ ክብር በሚቆጠርበት ዘመን ሴቶች ላሳዩት ታላቅ እምነት አድናቆቱን ቸሯቸዋል(ማቴ15:28 ሉቃ4:25-26 ከማቴ8:10 ጋር አነፃፅረው ይመልከቱ)፤ ሀጢያተኛ ተብለው የሚፈረጁ ሴቶችን በተለየ መልኩ ቀርቧቸዋል(ሉቃ7:36-50)፤ እንደ ሙሉ ሰው የማይቆጠሩትን ሴቶችን 'የአብርሀም ልጅ' በሚለው አይሁዳዊያን በሚኮሩበት መጠሪያ ጠርቷቸዋል(ሉቃ13:16)፤ እግዚአብሔር ሀጢያተኞችን እንደሚወድና ስለ እነርሱም ግድ እንደሚለው ለመግለፅ ራሱን በሴት በመመሰል ሀጢያተኞችንም በጠፋው ገንዘብ ወክሏል(ሉቃ15:8-9)፤ ከሁሉ በላይ በሚስት የምትመሰለውን ቤ/ክያን ህይወቱን እስከ መስጠት ድረስ በመውደድ ባሎች ሚስቶቻቸውን ህይወታቸውን እስከመስጠት ድረስ ሊያፈቅሩ እንደሚገባ ተግባራዊ አብነቱን ትቷል።

ይህ እንግዲህ የኢየሱስ አገልግሎት ነው። ነገር ግን የመሀመድስ አገልግሎት ከዚህ መመዘኛ አንፃር ፈተናውን ያልፋል ወይስ ይወድቃል? ....አስቀድሜ ቃል የገባኻቸውን ፅሁፎች ካቀረብኩ በኻላ እመለስበታለሁ።

ለማንኛውም የእኛ ጌታ ይህ ነው!!!

#ማጣቀሻ

1). 'መፅሀፍ ቅዱስ ምን ያስተምረናል?' ጥቅምት 2016 ገፅ.47 አሳታሚ መጠበቂያ ግንብ ድርጅት

(2). 'Understanding Jesus and Muhammed' Dr.Bernie Power, pg.103, 2016 Quoting Kohler Kaufmann, 'Pharisees' Jewish Encyclopedia.com

3). ዝኒከማሁ ገፅ.104, quote Korban Ha'eidah to Talmud Yerushalmi, Sotah3:4...

4).Discovering Biblical Equality' editors Ronald W.Pierce and Rebecca Merill Groothuis, Contributor Gordon Fee, ©2004, pg.129, quote Mishnah Ketubbot 1:8,7:6

(5). 'Can women be pastors/Elders in the Church?....' By Abera Awano Ajula, May 2018, pg.38